| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የዐሰቡን ፡ ፈንጇ ፥ ... ፡ ሳቡት ፡ እንጇ !" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ኅዳር ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2018-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## የዐሰቡን ፡ ፈንጇ ፥ ... ፡ ሳቡት ፡ እንጇ !



የውንብድና ፡ ዘመናቸው ፡ ወደ ፡ ፍጻሜው ፡ የተጠጋባቸው ፡ ኹለቱ ፡ መንደር-ገነኖች ፥ ኢሳይያስ ፡ አፈ-ወርቅ ፡ እና ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፥ ለዓመታት ፡ ሲዘጋጁለት ፡ የኖሩትን ፡ ሀገር ፡ በታኝ ፡ ጦርነት ፡ በዐሰብ ፡ ወደብ ፡ ሰበብ ፡ ሊያስነሡት ፡ ተቃርበዋል ። ይህ ፡ ተልእኳቸው ፡ እንጂ ፡ ከልባቸው ፡ ያነቁት ፡ ዐቅዳቸው ፡ አይደለምና ፥ ቀጣሪያቸው ፡ ምልክዮሽ ፡ ራሱ — በመላ ፡ ዓለም ፡ በተባባሰው ፡ ስያሳዊ ፡ መዘናበል ፡ ተደናግጦ ፡ በመተሻሸት ፡ ይመስላል — ዐቅዱን ፡ ሲከልስ ፡ እና ፡ ሲመልስ ፡ አዘግይቷቸዋል ።

ምልክዮሽ ፥ ለኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ የመራውን ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ ፡ ዐቅድ ፥ ወይ ፡ አንድ ፡ ፊቱን ፡ ርግፍ ፡ አድርጎ ፡ መተው ፥ አለዚያ ፡ ደግሞ ፡ ከያዘው ፡ አግጣጫ ፡ ዝንፍ ፡ ሳይል ፥ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ጸንቶ ፡ መፈጸም ፡ ይኖርበታል ። እሜዳው ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ወኪሎቹ ፡ እና ፡ የሰፈኑባቸው ፡ የውንብድና ፡ አገዛዞቻቸው ፡ ግን ፥ ተቀናቃኝ ፡ በዝቶባቸዋል ፥ ዕድሜም ፡ ተጫጭኗቸዋል ፥ በሙስናም ፡ ተደውየዋል ።

ምልክዮሽ ፥ ከመዠመሪያው ፡ የውሳኔ ፡ ማማረጫ ፡ ይልቅ ፡ ኹለተኛውን ፡ ማማረጫ ፡ ሳይከተል ፡ አይቀርም ፡ የሚለውን ፡ መላ-ምት ፡ አብዛኛው ፡ ለባሚ ፡ ይቀበለዋል ። ለዚህም ፡ ዋነኛው ፡ ምክንያት ፥ ከመቼውም ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፥ ዐምሐራ ፥ የተዳከመበት ፡ እና ፡ ወገን ፡ ያጣበት ፡ ይህ ፡ ታሪካዊ ፡ ወቅት ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹለተኛ ፡ ተመልሶ ፡ እንደማይመጣ ፡ ምልክዮሽ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ነው ።

ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ ምላጩን ፡ ሳቡት ፡ እና ፡ ይለይልና! ሀገር ፡ ኢትዮጵያም ፡ ትፈርስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ምልክዮሽም ፡ ምድረ ፡ ገነትን ፡ ይወርስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናያለን ። አጥፍቶ-ጠፊዎቹ ፡ መንደር-ገነኖችማ ፥ ገና ፡ ዱሮ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ሼጠዋልና ፥ "ሲመጣ ፡ ይመጣል" ፡ ብለው ፡ የሚመጣውን ፡ ኹሉ ፡ አስቀድመው ፡ በጸጋ ፡ ተቀብለውታል ፤ የታዘዙትን ፡ ይፈጽማሉ ።

"አፈንዱት!" የሚለው ፡ ትእዛዝ ፡ ሲመጣባቸው ፡ እና ፡ ሲያፈነዱትስ ፥ በበኩሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ምላሽ ፡ ይኖረዋል ፧ ባሥር ፡ አንጃዎች ፡ የተከፋፈለውስ ፡ የፋኖ ፡ ሰራዊት ፡ ተጠልፎ ፡ ለመሣሪያነት ፡ እንዳይውል ፡ ምን ፡ ዋስትና ፡ አለን ፧ እነዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ እና ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ጥያቄዎች ፡ ናቸው ፤ ዓለም ፡ በበኩሉ ፡ ወልወልን ፡ ያስታውስ ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

# ሥልጡንሕዝብና ።

www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።